

PDF

ብር 25.00
$15.00

ሀ ሞት

በ-ጎሮክ ሥጦታው

ሀ ሞት



በ- ጎሮክ ሥጦታው

(የግጥም ሥብስብ)

2005

ሀ᎓ሞት

የግጥም ስብስብ

በ ዜናክ ሥዮታው.



© ሄኖክ ሥዩታው ፤ ፳፻፩ (2005) ዓ.ም
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::

ለአስተያየትዎ፤
henoksitotaw@yahoo.com
https://www.henoksitotaw65@gmail.com

የሽፋን ምስል
ርዕስ ("You Tell Him the Tractor's Got an Oil Leak")
በ ሩ.ዱ.ድል (Roodoodle)



ማውጫ ገጽ

የነጋበት ማምሸት	10
ወፍና ማለዳ	11
የነፍስ ጀልባ	12
የዕድሜ ድውር	13
አሸባሪው ማነው?!	14
ረ-ሳድስ	15
ይሁዳ እምዘ እቡስ	16
የቶሎ ቶሎ ቤት	17
የቆሻሻ ወደብ	18
ተገለበጡ	19
የቱባ ከር ጫፎች	20
“ፍተላ”	21
የቆጥ ላይ ቅስቀሳ ፩	22
በራስ ምስል ዛቢያ	23
ጻፎች	24
ምንም ማለት ፍቅሬ	25
ለእኔዋ እጩ ሚስት	26
ከደዌው ዛፍ በታች	27
ጉጉት	28
ከራስ በላይ ንፋስ	29
እኔ ሠራሽ ሃውልት	30
አኻኻ ያመናል በለው	31
አርዝም አደንድን	32
የሸንታችን ውጤት	33
መንገድ	34
ሃውልቱ ይበላ	35

ማውጫ ገጽ

ምፅት 36
ቀን መቼ ይቆማል?! 37
የተዘጉ አንደበቶች 38
ጥላቻን በፍቅር 39
አባ ይፍቱኝ 40
ጥም የማይቆርጡ ዓመታት 41
ታሽጓል 42
እስኪበጠስ መጓተት 43
የተደበቀችቱ 44
ቅዥት 45
ዘነዘናና ሙቀጫ 47
ዝናብና ብቸኝነት 48
ወደድኩኝ ድጋሚ 49
የወደቀው ዘር 50
የሆድ አምላክ 51
በግ፣ሣር እና በግ 52
የመስከረም ናፍቆት 53
ሙሉ ጨረቃ በእኩለሌሊት 54
የራስ ምስል ፩ 55
ፍራ-ፍሬ 56
እችልሻለሁ 57
የቆጥ ላይ ቅስቀሳ ፪ 58
ስበት 59
አዳኝና ታዳኝ 60
ህምምታው ይታመቅ 61
የተዘጉ በሮች 62

ማውጫ ገጽ

መዘር በተጣርሶ 63
አምልኮ 64
ታቾቹ ተበሉ 65
የራስ ምስል ፪ 66
ድንቄም ሰንኮፍ ነቃይ 67
ጡት እንዴት ይጣላል 69
የራስ ምስል ፫ 70
እኔና እኔ 7ነ
ቀን በቀን 72
ይድረስ ለዱለኞች 73
የወህኒ ውስጥ ወህኒ 74
ትጠምቂልኝ ጀመር 75
የገደሉ አፋፍ 76
የሙተካካት ድግስ 77

መግቢያ

ዓለም ባያውቀውም ቅሉ፣ የሃበሻ ምድር ውሃ ብቻ ሳይሆን ግጥምና ቅኔም ያፈልቃል:: በአጭሩ፣ በሃገራችን ዘበናይ የግጥም ዘመን ተነበው የማይጠገቡ፣ ተመንዝረው የማያልቁ፣ ውብ እና ናዚራ ግጥሞችን አንብበን አጣጥመናል:: ጣዕመ-ቢሶችንም ታዝበናል::ታዝበንም ጆሮ ነፍገናል:: ግጥም በልክ የሚሰፉ፣ እንደ ገጣሚ ያለሀፍረት "ይህን ግጥም ለመጻፍ የበቃሁት...." ብለው ከ"ግጥማቸው" የባሰ አሰልቺ መግለጫ ሲሰጡ አይተናል ፤ ሰምተናል:: "ወቸጉድ"ም ብለናል:: ለአብሽ ለድንብላሉም ግጥም ሲያወርዱ ታዝበናል :: ይቅር ይበላቸው! ይቅር ይበለን ብለናል፤ ሆኖም ግን የግጥም ዘመን ይመጣል ስንል ተስፋ አድርገናል:: ግጥም ከነምልአቱ፣ በነፃነት የሚነግስበት ፍርሃት አልባ ዘመን እነሆ ሊመጣ ያለ ይመስለናል::

ገጣሚ ነፃ ነው:: ሃይማኖቱም ነፃነት ነው:: ስለሚጽፈው ነገር ነጋሪ፣መካሪ፣ኢጋጅ እና መሪ አያሻውም:: የተሰማውን በእውነትና በውበት አበጃጅቶ ይጽፋል:: ሲራሊዮናዊው ገጣሚ አመር ፋሩክ ሲሴ (I write what I feel) በተሰኘ ግጥሙ እንዳለው :-

...No one feels what I write
No one tells me what I write
I write what I feel.

ዘመናችንም ነጋሪ የማይሹ ገጣሚያን ትፈልጋለች :: ያለፈውን ፈለግ በመከተል የራሱን የማያጣ ፤ የራሱን ሃሳብ ድንበር ሳይከልለው ፤ ፍርሃት ሳይሸብበው የሚያፈነዳ "አዲስ" የግጥም ትውልድ ያሻናል:: ደግሞ እየመጣ ያለ ይመስለኛል :: ግጥም ማለት የሕይወትን ልስላሴ ብቻ ሳይሆን ሻካራዋንም ፤ ጣዕሚን ብቻ ሳይሆን ምሬቷንም ፤ ብርሃኗን ብቻ ሳይሆን ጭለማዋንም

ቄለማዋንም የሚገልጽ ኃያል ሣበብ እንደሆነ የሚያሳይ ጠቢብ ያሻናል። እንደ ብዙዎቹ የቅኝ ዘመን የአፍሪካ ሥነ-ጽሑፎች ገፀ-ባሕርያቹ በቀደዱለት የስልት ቦይ የሚይፈስ "ኦሪጅናል" ግጥም ማንበብ ተጠምተናል፤ ዘመኑም ሊመጣ ያለ ይመስለኛል ። ከዚህ በማጎንቆል ላይ ያለ ዘመን ውስጥ ለማበብ ከሚውተረተሩና "አይነኬውን" በድፍረት የነኩ ገጣሚያን መካከልም ሄኖክ ሥጦታው አንዱ ነው። ለኔ።

ግጥም ትኩሳትን ትሻለች። ገጣሚው ቃላትን በንዝረት፣ በምትሃት፣ በውበት እና እውነት አበጃጅቶ ሙዚቃን በግጥማዊ ስልት ይፈጥርልናል። ቁስልን ማከም፣ ተስፋን ማለምለም፣ ረመጥን መቆስቆስ የገጣሚው ሚና ነው። በቃላት ማከምና መፈወስ ነው ፤ግጥም። ሄኖክ በዚህ ተከናኗል። ለሚመርጣቸው ቃላትና ለምት የሚገደውን ያህል፣ ለሚያነሳው ሃሳብ ግን ቅንጣት ፍርሃትና ማመንታት አይነካካውም። የግጥም ነባር የርዕሰ ጉዳይ አዙሪት (Vicious Circle) ጥሶ ወደሌላ አውታር ተሻግሯል።

'ግጥም አወዳሽና አልቃሽ ብቻ ሳይሆን ሽንቋጭም ነው ለካ ' ያስብለናል። ለምን ብቻ ፍቅር? ለምንስ እንጉርጉሮ? እያሰኝ ወደ አይነኬው ርዕሰ ጉዳይ በድፍረት ያሸጋግረናል። ዳር ዳሩን ብቻ ስናነው የኖርነውን ቁስል ንፋስ ያስመታልናል። ዘልማዳዊ ከሆነው ዙሪያውን የማከክ ብያኔ ያላቅቀናል። አሰይ! ካሰቡ አይቀር በነባት፣ ከዳሩም አይቀር በድፍረት እንዲህ ነው። "የምጽፈውን ማንም አይነግረኝም" እንዳለው ፋሩክ ሲሴ፣ ሄኖክም ያለነጋሪ ይጽፋል። እንዲህ፦

ተከፍቷል ይሉናል፤ ኢትዮጵያ በሮቿ፤
ተዘግቶ ቆመናል ፣ አሁንም ልጆቿ።
አጥር ዘሎ መውጣት፣
ወንጀል ነው ይሉናል፤
አፎች ቢከፈቱም፤ በሩ ግን ተዘግቷል።
ከመካከላችን፣ አጥሩን የደፈሩ፤
ጥቂቶች ቢያመልጡም፣
ብዙዎች ታሰሩ።
እኛ ፊሪዎቹ፣ ለሕግ የተገዛን፣



በራሳችን አገር፣
መውጫ - መግቢያ ያጣን፤
ማንኳኳት አልተውን፣
ወይ አልሄድን ጥለን፤
በቁቢጸ - ተስፋ፣ ታስረን በምን አልባት
አሁንስ ታነተን፤ በር በሩን ማየት።
አትበሉ "ነፍት ነው" ፣ በሮች ተቆልፈውም፤
ካልሆነም እንድፈር፣ ቅዕሩን እንዝለለው።

በሃሳብ አናት ላይ እግሮቹን አንፈራጠ *መግቢያና መውጫ* በሚከለክል *ማሕበረ - ፖለቲካዊ ሥርዓት ሥር* ተጠፍሮ ለሚኖር ገጣሚ ወዮለት ! ከዚህ አስራት ተላቆ የነፃነት ውልድ ግጥሞቹን ለማውጣት አቤት ያለበት *መከራ*? ! . . . ዛሂያ በነባር ወግና ስርዓት ተሸብቦ *መኖር* ያንገፈገፈው ገጣሚ በነፃነት *መንፈስ* የተለከሰ ዕለት ማን *ይመ*ልሰዋል ! ?

ተከብሮ የኖረውን የግጥም ቅዕር ጥሶ የሃስብና የቃላት ነፃነት ያወጀ ገጣሚ ዕጣው ምንም ይሁን ምን ከአስራት ነፃነቱን ያስበልጣል። እንግዲህ ሄኖክም "ሀ - ሞት" ሲል በሰየማቸው ስብስቦቹ ‘ሆ ያሉ ’ለት የስውቀትን ዕፀ - በለስ ቀምሰዋልና ሞት እንደሚከተል እያወቀው ፣ ‘ሆ የፊደል ብቻ ሳይሆን የድፍረት /የነፃነት/ ፣ *መጀመሪያ* መሆኑ እየገባው ፣ "ህሞት" የመጌ *ቅመም መ*ሆኑ እየሰረፀው እነሆ ቆፍጣና ግጥሞቹን ሸልሞናል። ለአድናቆቱም፣ ለወቀሳውም "ሀ - ሞት" የተሞላ ሂስ እንደሚጠብቀው እያወቀ የድርሻውን አበርክቷል። በጋዜጣ ብቻ ሳይሆን በግጥምም ሃሳብን በነፃነት *መግለ*ፅ እንደሚቻል ጭላንጭሉን አሳይቶናል። እኔ የተሰማኝና እንዲህ አልኩ። እናንተም የበኩላችሁን በሉ።

ጋዜጠኛ ገዛኸኝ *መ*ላኩን

*የነጋበት ማምሸት
ወይስ
(የመሸበት ማደር?)

"እውነትን ተናግሮ፣ የመሸበት ማደር"
መባሉን ሰምተናል፤ ትውፊቱ ሲነገር።
ዛሬ ጊዜው ከፍቶ፣ ሰንታይ የኮሪጥ
እውነቱን ተናግሮ፣ አይረባም መጋፈጥ።
የመሸበት ማደር፣ ቀርቷል ትላንትና
እውነት ተናጋሪን፣ ማን ያስመሸውና?!
እንዲህ ሆኗል ዛሬ፣ ተረቱ ሲለወጥ
"እውነት የሚናገር፣ እንዳወራ ያምልጥ!"

ሰኔ 19 ቀን
2004 ዓ.ም

*ወፍ እና ማለዳ

እንኳንስ ችግኙ፣ ሰዎች የተከሉት
ሥር ይይዝ ነበረ፣ አዕዋፍ የዘሩት።
ዘንድሮ ግን ወፎች፣ እንኳንስ ሊዘሩ
ናፍቆሻል ማለዳ፣ መስማት ሲዘምሩ።

ወፎች ከማለዳ -
በምን ተቃቃሩ?!
ዕለመቱ ሲገፈፍ -
እንዳለበሠሩ፤
ማዜም ተስኗቸው -
ተዘግቶ ጀንበሩ
ወደማነጋበት -
ወይትስ በረሩ?!

መሰከረም
17 ቀን 2002ዓ.ም

*የነፍሥ ጀልባ

ከፊት ለፊት ወደብ አለ፤
ከሸ. ማይል ሸ. አርቆ -
ባሕር ቀዝፎ ለሚጋፈጥ፣
ለሚነሳ ማዕን አውቆ።
በስተጀርባም ንፋስ አለ፣
ለሚጋፈጥ ባሕር ዘልቆ፤
ይወቅ ብቻ መድረሻውን፣
ያሸንፋል ቀን ጠብቆ።

*የዕድሜ ድውር

የ፣ ድሜ ድውር፣
ልቃቂት ነን
ባንድ ጉድጓድ
፣ ምንሸመን።
ተተርትረን፣
ቀን ከለሊት . . .
ልቃቂት ነን ፣ ምንፈታ፤
አሥከሚቋጭ ተፈዕመን . . .
የሸማኔው አዲስ ኩታ።

*አሸባሪው ማነው?

በቀይዋ ብስራ፣ የነተብኩት ሁሉ፤
አንዴ ነኔ ወጥቷልኝ አስቲ ተቀበሉ።
እውነትን ሊናገር፣ አፉን የነፈተ፤
ንቅዘቶችን ነቅሶ፣ ድክመትን ያተተ፤
በዚህች ጉስቁል አገር፣ ምሣር በበዛበት፤
በሚቀጥለው ቀን፣ ለርሡ ወየውለት!!
ለምን!?
ፊራጅ ነው ዘራፊ፤ ተዘራፊው ሌባ
ትኞት ያሳስራል፤ በማሸበር ደባ።
የታል!?
"ነፃ አውጪው" የታል!?
ሆኗል ጨቋኝ መሪ
"ለምን" ባዩን ፊራጅ፤ "በሽብር ፈጣሪ"
ደፍሮ የሚናገር፣ ዘብጥያ ታሣሪ።
ማነው!?
ዐረ-ሠላም ማነው!? ማነውስ ነፃ አውጪ!?
አሸባሪው ማነው!? ማንኛው ነው ቀጪ!?
ወንጀለኛው ማነው!? ማነውስ ታሳሪ!?
ዐረ-ሠላም ነሣሽ! አራሡ መስካሪ
"ለምን" ባይ ተነሣሽ፤ ላገር ተቆርቋሪ!!

2004 ዓ.ም

ረ - ሳድስ

የነበረው ነበር፣ ያልነበር አልነበር
ያልነበረው ነበር፣ ነብሮም አልነበር።
አልነበረም ነበር፣ የነበረው ነገር
የነበረው ነገ፣ር አልነበረም ነበር።
ካልነበርው ነገር፣ የነበር ቁም - ነገር
ያ ሁሉ ቁም - ነገር፣ አልነበረም ነበር።
እንዲህም አልነበር፣ ያልነበረ ነገር
ያልነበረ ነገር፣ እንደዚህም ነበር።
ነበርና ነገር፣ ነገርና ነበር
ከነበር፣ ካልነበር - ካልነገር ከነገር
(በምናቤ ዳራ)
ተጣርሰውም ነበር፤ ተዋደውም ነበር።

2005 ዓ.ም

*ይሁዳ እምዘ አቡስ

ይሁዳ "ታማኙ" እውቁ ደቀ መዝሙር፣
ተከትሎ ሲሄድ ታላቁን መምህር፤
ከመሐከላቸው፣ እንዲፈፀም ቃሉ፣
ጠንክሮ ሲማስን፣ ሌሎቹ የታሉ? !
መሲሁ ደጋግሞ፣ እንዳስተማራቸው፣
ሞቶ በሰልስቱ፣ ይነሳል ላሳቸው፣
መሞኔ ትንቢቶች፣ ለመተግበራቸው፤
ከሰንቱ ተከታይ፣ የተጋው አጥብቆ፣
አንድ ብቻ ነበር፣
አሱም ሞቱ ታንቆ።
እ - ና - ም
ጊታውን ሊሸጠው፣ እንዲያ የጓጓበት፣
ከዲናሩ ሌላ፣ ቢኖር እንጂ አውነት፣
ለቃሉ መፈፀም፣ ቁዳ ባልሆነለት !

*የቶሎ ቶሎ
ቤት

በፍራሽ አፈር አብዙቹ
የንቃይ ጣሪያ ወትቹ
ገባሁና "ቤት" ሠርቹ፤
ካፊያ ሲጥል አፈሰሰ
ወኞ ከረምቱ ተጋወሰ?
ተገንብቶ በፈረሰ።

1998 ዓ.ም

*የቆሻሻ ወደብ

የሰልጣኔ ዝቅጥ መጣያ፣ የጥራጊያቸው ወደብ ነን፤
የጣሉትን የምንለቅም፣ ካልጣሉልን የምንለምን፤
ፊረስም ነን ለነዚሁ፣ እንዳሻቸው የሚያደርጉን፤
ካሻቸው የሚለጉሙ፣ ካሻቸውም የሚጋልቡን፤
ካሻቸው የሚጭኑ፤ ካሻቸውም የሚዋጉብን።
የገደልም ማሚቶዎች ነን፤ የፉጨቱትን የምንደግም፤
በለኮሱት ስንቃጠል፤ በቃ ሲሉን የምንከሰም!
በስማ በለው ተብትበው፣ "በቁሳቸው" እንዳጨቁን፣
ስንዳከር ዳናው ጠፍቶን፣ እስከ መቼ እንዘልቃለን!?
ሲጋልቡን ስንጋለብ፣ ሲጭኑንንም ስንሸከም፤
የጣሉትን ስንለቅም፣ የሚሉትን ስንደግም!
እንደ አራስ ልጅ በሰው ጀርባ
እስከ መቼስ እንዘልቃለን!?
እስከመቼስ እንከርማለን!?

መስከረም - 2005 ዓ.ም

*ተ-ገለበጡ

እነሡማ!
እ—ኑ—ማ?!
ዶክተሮቹ፣
ኢንጂነሮቹ፣
ፕሮፌሰሮቹ፣
አቶዎቹ . . . !
ምን ሆኑ?!
ሲቆሙ
ተቋቋሙ፤
ሲያብሩ፣
ተባበሩ፤
ከ—ሀ—ሥ?!
ሲደገሩ፣
ተጋሩ፤
ሲጋሩ፣
ተደናቀፉ!
ከ—ሀ—ሥ?!
ሲታሰሩ፣
ተባበሩ፤
ሲፈቱ፣
ተፋቱ፤
ሲጋመሡ፣
ታመሡ፣
ተካሰሡ።
ኋ—ላ—ሥ?!
አጋማሹ፣
ጥለው ሸሹ፤
ካገር ወጡ
ቀሪዎቹሥ?!
!ቪ-ሠሀሃ፤-ሁ

1999

* "የቱባ ክር ጫፎች"

ጥምጣመ - ውሥብሥብ፣ ሕይወት እንደ ድውር፤
ጫፉን ለመያዝ ነው፣ የሰው ልጅ የሚጥር።
የተጠቀለለው . . . መፈታት ሲጀምር፣
መልሰህ ጠቅልለው፤ ተተብትቦ እዳይቀር።
የለውም ጫፍ ብሎ - ቆርቦ የሚጀምር፣
አራት ጫፍ ያገኛል፣ ክሩን ሲተረትር።
ጫፍ መያዝ በጥሶ፤ በጥሶ መቋጠር
ኢትዮጵያን አርኅታልኝ፤ የብዙ ጫፍ ሀገር።
ሞልቷታል እምዬ - አያልቅም ቢቆጠር፣
አያሌ ጫፍ ወራጅ፣ ዕልፍ ቆርቦ - ጀምር፣
ተብትቦ የሚተው፣ ደህንኛውን ድውር፤
ለመፍታት ሲነሳ ጠቅሎ እማይጀምር።

ሰኔ 12/ 2004 ዓ.ም

* "ፍተላ"

እንቶኔ ከበረ። እንዴትሰ ከበረ?
እንቶኔ ከሰረ። እንዴትሰ ከሰረ?
ውሃ ስንት ገባ? ኬርሲን ፈሐመረ?
ባለብሩ ዳቦ እውነት ድሮ ቀረ?
እያልኩኝ ሰፈትል ሳጠቁር ሳቀላ
የንሮን ውድነት በአልኮል ሳሰላ
በሞቅታ መንፈስ ያገኘሁት መላ
"ከውሃ ይረክሳል የእኛ ሰፈር ጠላ"።

06-08-2005ዓ.ም

*የቆጥ ላይ ቅስቀሳ ፩

ነግቷል ! ነግቷል ! ነግቷል !

ይሉናል፣

ይሉናል፣

ይወተውቱናል !

ተነሡ - ተነሡ - ተነሡ !

ይፈክሻሉ እነሡ

እየቀሰቀሱ . . . ።

ተቀስቅሰን በፈጠኘነቱ

ተበስሮልን ቀን መንጋቱ፤

አደባባይ ስንወጣ

ቀስቃሻችን ነየት ይምጣ ! ?

ግንቦት 1997

*በራስ ምስል ዛቢያ

ልጅ ሆኜ ነበረ ያደረብኝ ፍቅሩ
ዝናብ እና ምሽት
ካፊያና ነጎድጓድ በአንድ ሲጣመሩ
በእንቅልፌ ሰመመን እያየሁ ሲዳሩ
ያሸለብኩኝ እለት
ቅዠቴ ጣፋጭ ነው ጥሁም ነው አዳሩ።
ለአቅመ - አዳም በቅቼ ከጎኔም ሰው ኖሮ
ዝናባማ ምሽት ማፍቀሬ ጨምሮ
ጨለማ ሲያረብብ ደመናው ተቋጥሮ
እናፍቅ ነበረ ማየት ሰማይ ጠቁሮ።
ጮርቃነቴ የታል? የታል ልጅነቴ?
ጓደኞቼም የሉ ሰው የለም ከቤቴ
መታሰሬን ባዩ በብቸኝነቴ
ህመሜን ባዩልኝ
ጭንቀቴን ባዩልኝ
ናፍቆቴን ባዩልኝ
መሸቶ ዝናብ ሲጥል
ከራሴ ስጣላ በስቃዬ ስዝል
ምን እንደምመስል።

1998ዓ.ም

*ጻፎች

አወይ እኒያ ጻፎች፣ ሥልጡኖች በሜራ
እነሱ ሲያፈርሱ፣ መሲሑ ሲሠራ፤
ከሞት እንቅልፍ ላይ፣ አልዓዛር ሲጠራ
ሞቱን ደገሱለት፣ ጠበቀው መከራ።

* * *

ዛሬም በአውሉ፣ አልፍ ጻፎች አሉ
መስለው አውነት ወዳድ፣
አውነት የገደሉ፤
እንደነዚያ ጻፎች፣
ማሜር የተካኑ
ሃቅን አያበ-ሉ
የሚያድፈነፍኑ።
ከወጡበት መንበር፣ በያዙት አውቅና
ቆመናል ባሉቱ፣ ለአውነት ጥብቅና፤
ምን ያህሉ ናቸው የተጨፈለቁት? !
እግራቸው ተነሰቶ፣ ይታይ የረገጡት !

* * *

እናም - እኒያ ጻፎች፣ አውነትን ሊያጠፉ
ከፋት ከመጠንሰስ፣ ከቶም አላረፉ።
ሺህ ሜራ ቢሸረብ፣ ሺህ ጉድጓድ ቢቆፈር
ሕያው . . . ቢገደልም
መነሣቱ አይቀር።

*ምንም ማለት ፍቅሬ

ምንም በሌለበት ምንምን ሰንቄ
ስቃይን አተረፍኩ አንድ አንቺን ናፍቄ።

መናፈቅ ! ?

ናፍቆት የጥንት ወዳጅ፣ አዲስም አይደለም
በሽታ ሆነ እንጂ ከምንም ጋር ሲገጥም።

ምንም ! ?

ከምንም ጋር መግጠም መች ሆነ በኩሬ
አፈቅረው ነበረ ፤ ካንቺ በፊት ፍቅሬ።

በፊት ! ?

(በፊትማ ፊት ነው፣ ካንቺ የቀደመ)
ሰው ሳገኝ ስከዳው ፣ ስከዳው ሰው ሳገኝ
ስመለስ ሰው ሳጣ፣ ስመለስ ያልከዳኝ።
እና ምንም ማለት ፥-
በመናፈቅ ምናብ፣ ከራሮ ስቀጣ ፣
ላገኝ ብዬ ጥዬው፣ ያገኘሁት ሳጣ ፤
እሱ ነው ምንጫ ፣ስቃዬን ያስረሳ፣ ናፍቆቴን የሻረ
እስከመለስ ድረስ ፣ ከአለበት ፀንቶ፣ ጠብቆኝ የኖረ።

2005ዓ.ም

*ለኔዋ እጩ ሚስት

ከፈላጊሽ ለመቃጠር ፍቃድሽ ሆኖ ሳለ
ልቤ እንዴት ይመንሽ፤ "እመነኝ" ስለተባለ?!
ሰበብ የግልሽ እንደሆን . . . ርዕቱእነትም የግልሽ
ባልሽው ብረታም እንኳ፤ ያመንኩሽ ግን እንዳይመስልሽ።
በተጫራች ማስድ ግብግቦ፣ ይጨናነቅ ሆድሽ ይመላ
በልተሽ ስትጨርሽ ግን እንዳትመጪ በኋላ!

28-08-05 ዓ.ም

*ከደዌው ዛፍ በታች

ሐጺላጺ የግለቸው፤ ሐፍስ እመ ታፈቅሩ
ለነፍሳቸው ቆሙ ስንል፤ ለግለቸው በዘ ገብሩ።
አማኝ በዝቶ በተረፋትት፤ በዝ ' ች ጉስቁል ሀገራችን
ከደዌው ዛፍ ለመጠጋት፤ የድሃ ቸር መሆናችን
የገቢ ምንጭ ሆኗል ለካ፣ ኖርን ስንል ለነፍሳችን።

*ጉጉት

ከአርሞኞች መሐል፣
አርግብ ተመስላ፤
"አርግብ ናት"
ያልናቱ፣
ላባ ተከልላ፤
ሥትከፍተው አፏን፣
አየን ጥርሥ አብቅላ።

የካቲት
20 ቀን 1998 ዓ.ም

*ከራስ በላይንፋሥ

ብዙ ልቦች ሰው አላቸው፣ የለም ባዶ - የለም ወና !
ብዙ ልቦች ሰፊ ናቸው፣ብ—ዙ ይዘው ቀርቷል ገና፤
የአንድ ሰው መሆን የለም፣
"የኔ" ማለት ቀረ ድሮ
በ"ምን አለው" ተተክቷል፣
' ያንድ መሆን "አይደል ኑሮ" ¡
ልቦች ሰፍተው እንዳ ' ዳራሽ፣ ዝኪ ወጪው ተበራክቶ
እንደ እንከፍ እየታየ፣ የሚያፈቀር ካንዱ ዐንቶ፤
"የኔ" ሚባል - ብቸኛ ሰው፣ ከራስ በላይ ከየት መጥቶ ! ?

*እኔ ሠራሽ ሐውልት

በመልካም ሥራችሁ፣ የጣትታወሱ
የኋላ . . . የኋላ፣ ስለምትረሱ፤
በሕይወት ሳላችሁ፣
ይቁም ሐውልታችሁ፣
ይጠራ ስማችሁ ፤
ከሌላችሁ የለም፣ ከብረ - መወድሱ
ከትላንት ተማሩ፣ ታሪክን አትርሱ።
ለውዳሴ ከንቱ፣
ሐውልቱን ያሠራ
መንገድን ሰይሞ፣
በስሙ ያስጠራ፤
ታሪክን ለመቅደም፣ የተሸቀዳደመ
ነውና ፣ ሚቆመው፣ እርሱ እስከቆመ።

*አኻኻ ያመናል በለው!

"አኻኻ ያመናል ገና!
አኻኻ ያመናል ገና!
ያመናል ገና!
ያመናል ገና!
አኻኻ ያመናል በለው!
አኻኻ ያመናል በለው!
ያመናል በለው!
ያመናል በለው!"

እስከ መቼ ነው ' ምንታገሰው!?
ብሦታችንን የምናፍነው!?

"አኻኻ ያመናል በለው!
ያመናል በለው!
ያመናል በለው!"

ታፍነው ኖረው የነረመጥ፤
ነባ ወጥተዋል ከጎረቤት።

"አኻኻ ያመናል በለው!
አኻኻ ያመናል በለው!
ያመናል በለው!
ያመናል በለው!"

መጪቆናችን መቼ ቀለለ!?
ከትላንት ዛሬ ብሦ ቀጠለ!
"አኻኻ" ማለት ሁሉም ከቻለ
ነባ ለመውጣት ብንሞት ምን አለ!?!
እንዳናየሁትኝ ከጎረቤቱ
"አኻኻ" ሲባል አይቀር ማለቱ።

ሐምሌ15/2004ዓ.ም

*አርዝም አደንድን

ስሜት ልጓም በጠሰ፤ አስማት ዋለ ለምንዝር
በአርዝም አደንድን ድግምት፣ አቅም ተሰዋ ለግትር።
መስዋቱ ባልከፋ፣ ለዚያችኛዋ (<<ቂንጥር>>)
አስማት ስሜት ታቅፎ፣ ካሸንፈው ያስማት ቀመር
ወንድነቱን ከደ.ልና ፣ ቀድሞውንም ወንድ አልነበር።

23-08-2005ዓ.ም

*የሽንታችን ውጤት

የሰርፋችን ውጤት፣ ፈጠረ ዕየፋ
ትላንት የሸናነው፣ ዛሬ ላይ ከረፋ!
በነውራችን ብዛት፣ መሬት ተበከለ
የሽንታችን ውጤት፣ ሣማ አበቀለ
ቅጠሉ መልሦ፣ እኛን አቃጠለ።

2004 ዓ.ም

*መንገድ

ወጪ ወራጅ በበዛበት፣
በዚያ የሕይወት ጎዳና
እውነት ፍለጋ ሲባዝን፣
ልቤን ተርፎት ጣመና፤
ከሚንዱ ላይ አረፍ ሲል
ከወደቀ ዋርካ ደርሶ
ሲፈልገው እንዳልኖረ፣
የጠየቀው ተመልሶ
ዋርካው እውነት ሆነለት፣
መንገዱ ላይ ተገርስሶ።

ሃውልቱ ይበላ

የዳቦውን ዋጋ፣ አራከሶ ከጠጠር
ሲበላ ለኖረ ፣ ቃርሚያ እንኳን ሳያስቀር
የጥንት ጥጋባችን፣ በተረት ይዘከር።
ዛሬም ሀዘን ላይ ነው፣ "እርም" አልበላም አገር
በልተው ባይጨርሱት፣ "ድንጋይ ዳቦ ነበር" !

ድንጋይ ሆነ ዳቦ ፣ እነዚህ ሁለቱ
ከሰውነት በላይ፣ ተከብረው ማየቱ
ራስ መሸንገያ የሆነን ቅሪቱ
ታሪክን አይመስክር ተረት ምንአባቱ !
ርሃብ ከጠና ይበላል ሃውልቱ።
እንዲህ ነው ነገሩ . . .
ኮሶ እያጠጡት "ማር ነው" የተባለ
ሀሞት ያጣጥማል ከብርዝ የተሻለ።
ተረት ያናወዘው፣ ይህ ነው የኛ ኑሮ
ኮሶ እየጠጣን፣ መመኘት ነው ደሮ ።

ምንም እውነት የለ ፣ ከዚህም የባሰ
ድንጋዩ ተወደ ፣ ሰው ነው የረከሰ !

01-09-05 ዓ.ም

***ምፀት**

ያረጀው ሊታደስ የግድ ሆኖ ሳለ
ከፈረሰ ወዲህ፣ "ይፈርሳል" ተባለ።
ምፀት!
ድርጊት ውሎ ሲያድር፣ ታሪክ እንደሆነ
ታሪክን አፍርሶ፣ ታሪክ ተወጠነ።
ምፀት!
ከትውልድ መንደሬ አልነሳም ያለ
"እሳት" ነው መፍትሄው፣ ይኸው ተቃጠለ!
ምፀት!
ፈርቆስ ተቃጠለ
ያው ተምበለበለ . . .
በቅሎ ቤት ነደደ
ኮልፌ ቄስ ወለደ
አዲስ አበባ አመደ . . .
.....
.....
.....

መቃጠልን ፈርቶ ሰላም የወደደ
እሳትን ፍራቻ ስንቱ ተሰደደ??

2005 ዓ/ም

***ቀን መቼ ይቆማል?**

ሕጓ ለውጥ ሆኖ፣ ዓለም ስትፈጠር
ተጓዥ አድርጋ ነው፣ ማንም ቆሞ ‘ማይቀር።
ቀን ቆሞ አልቆምን፣ ቆመን ቀን አልቆመ
ተጉዘን ስንደከም፣ ሲጓዝ አልደከመ።
ለውጣችን በእጁ ነው፣ መች እጃችን ገባ!?
ቋሚ ሰውስ የታል፣ ከለውጥ ያልተጣባ!?
ከዕድሜ ሠረገላው፣ ይዞን ከሚከንፈው
ካሰረን ሠንሰለት፣ በሞት ከሚፈታው
እራሱን ያስጣለ፣ የታለ ቋሚ ሰው!?

*የተዘጉ አንደበቶች

1ኛው ቀን
ዓይት - ዓየችው
ዘጋት - ዘጋችው !
ቤቱ ገባ፤ ቤቷ ገባች
በሩን ዘጋ፤ በሯን ዘጋች !
መሸ ፤ ነጋ
2ኛው ቀን -
እሱም ወጣ፤ እሷም ወጣች
እሱም ዓይት፤ እሷም ዓየች
ኮራ . . . ኮራች፤
እንዳላያት፤ እንዳላየች
ሄደ . . . ሄደች።
3ኛው ቀን -
4ኛው ቀን -
5ኛው ወር -
6ኛው ወር . . .
ለውጥ የለም፤ ለውጥ አለ፤
ምንም የለም፤ ምንም አለ !
በተዘጉ አንደበቶች፣
ለግባቡበት የቀለለ
የቀኖት መንገድ አለ።
በዝምታ ሚግባቡበት . . .
ፈጥረው ነበር
አንድ ነገር
ለሌላ ሰው ፣ ማይነገር።

*ጥላቻን በፍቅር

ማፍቀርን መች ሸሸው!?
መች ተዘጋ ልቤ!?
ከመሮጥ መች ቦዘንኩ
መች ፀዳሁ ታጥቤ!?
መፈቀር መች ጠላሁ?
መች አረፈ ቀልቤ!?
ቁንጣን መች ወጠረኝ!?
መች ተፋሁ ጠግቤ!?
ነፍስ የዘራሁበት፣
ማይንኳኳ በራ
መሸቶ ነግቷል ዛራ፣
ነግቶም መሸቷል ዛራ።
ብራብ በሰው ገላ፣
ቢወልፈኝ ጠኔ፣
በችጋር አልሞትም፣
አልደረሰም ቀኔ!

የካቲት
27 ቀን 1998 ዓ.ም

*አባ ይፍቱኝ

"አባታችን" የምላቸው፣
ከህሃትን የለበሱ
ሃይማኖትን አሰያቡ፣
ቤተ - መቅደስ አረከሱ።
ያልኩት . . .
እስከዛሬ ሲያስተምሩን፣
የሰማነው ከስብከቱ
"ለአምላክ መንግሥት፣
መብቃት ማለት . . .
የዘላለም ታላቅ ሹመት
ዓለም ጠፊ፣ ምድር ከንቱ"
እንዳላሉን ቀሳውስቱ . . .
ያልኩት . . .
ለሰው ኃጢአት እንዳልያሙ
ለሠላም ዘብ እንዳልቆሙ፤
ጉባኤውን አጎደፉ
በዓለም ፍቅር ተሸነፉ።
ያልኩት . . .
ለጥቅማቸው ሲሻኮቱ
በኔ ልብለ ሲራኮቱ፤
እርስ በ ' ራስ የታመሱ፣
ለመስቀሉ አልነበረም -
ጳጳስቱ ጦር ያነሱ !
ያልኩት . . .
እኔ ነኝ
አባ ይፍቱኝ።

ሰኔ
20 ቀን 2001 ዓ.ም

*ጥም የማይቆርጡ
ዓመታት

ሕይወት ስትደግስ፣ ታዳሚ ነንና
"ብሉልኝ" ልትለን፣ ማዕጁን ከሸና
ተጨንቃ ተጠብባ፣ ከጨውና ቅመምም፣
አዋህዳ ወጧን፣ በጥም እና ጣዕም፤
በልተን ስንጠግ፣ ደግሞ ልንጠጣ
ጠጥተን ላንረካ፣ ጥማችን ላይወጣ!
ሀዘን'ና ፌሽታው፣ ጥላቻ'ና ፍቅር
ማግኘት'ና ማጣት፣ የዚህ ሁሉ ምስጢር
በዓለም ስንኖር፣
አንዲጠግን ነበር።

*ታሸንል

ቢጠሩት ላይሰማ፣
ልቤ ተጠርቅሞ
የሚያንኳኳው ማነው፣
ደጃፉ ላይ ቆሞ? !

*እስኪበጠስ መጓተት

እስከዛሬ የተጓዝነው፣ ሁለት ሆነን ባንድ መንገድ፤
በወለድነው ፍቅር ነበር፣ ባቄራኝን ኃያል መውደድ።
እንደዛሬ ሳይወጠር፣ ፍቅር በዕልህ ተሸንፎ፤
ሲያናቁረን ቀን ተሌሊት፣ ቅራኔያችን እጅግ ገዝፎ፤
እስኪበጠስ ሳንጓተት፣ ሲቻል መፍታት በቀላሉ፤
ከመቋሰል የዘለለ፣ ምን ፈየደ መታገሉ?!

1997ዓ.ም

***የተደበቀችቱ**

አደን ሽሽት ተደበቅኩ
ተፈጥሮዬን ግን አልገደልኩ፤
ግና ከተደበኩበት ሳለሁ
የተሸሸገች ቆንጆ አየሁ፤
"የምርጥ አዳኝ ብቃቱ
ሳይሆን ሌሊት ማድባቱ
ቀን የሸሸጋትን ማግኘቱ!"

2005 ዓ.ም

*ቅዥት

የህልም ዓለምን ሳካልል፣
በቁም ሳለሁ ተኝቼ
ከወደቅሁበት ፀሊም ዓለም፣
ሳልፈልገው ተገፍቼ፤
እንደ ለሊቱ ቅዥቴ፣
መሮጥ ተስኖት እግሬ
ሳልፈልገው ተተብትቤ፣
እግር - ተወርች ታሥሬ፤
ልክ እንደዚያው ቅዥቴ፣
በቁም ታፍኖ እንደበቴ
እንዳለመልጥ ከዕሥራቴ፣
በኖ ጠፋና ብርታቴ . . .
ዘመኔን በግድ አቅፌ
በታ እንዳልል ጋት አልፌ
ተወግቼ አንዳች መርፌ፤
ተውሰብስቤ በዕልፍ ቅዥት
ስንቱን ዓለም አካለልኩት? !
መሬት ለመሬት ስንፏቀቅ፣
ሰማየ - ሰማያት ስንሳፈፍ
ድንገት መጋለብ ጀምሬ
ድንገት ባሕር ስቀዝፍ

የማፈቅረው፤ ግን ያጣሁት፤
የምመኘው፤ ግን ያልኖርኩት
የምጠላው፤ ግን የሆንኩት!
ትላንት ቅዥት፣ ዛሬ ቅዥት
መኖር ቅዥት፣
ያሻሁትን ብቃዠውም፤
ቅዥቴን ግን አልኖረውም
የኖርኩትን አልቃዠውም!

መጋቢት
28 ቀን 1999ዓ.ም

*ዘነዘና እና ሙቀጫ

በዘነዘናና ሙቀጫ መሃል
እናውቃለን ተሸክሸኳል፤
የአጋጣሚ ነገር . . .
ተወቅጦ ሳይበቃው
ዛሬ ተገለግሎ ነጥሮ ከሙቀጫው
እድል ያልቀናቸው ሌሎች ሲወቀጡ
እርሱ በወጣበት ነጥረው እንዳይወጡ
ሙቀጫው ይቦርቦር - ይስፋ አለ ከቂጡ።

1999ዓ.ም

*ዝናብ'ና ብቸኝነት

መዝነቡን ቢጀምር፣ ሰማይ በ'ሳት ታርሶ
ነጐድጓድ ከንፋስ፣ ወልዶት በተጣርሶ፤
ይበርደዋል ብዬ፣ ሙቀትን ፍለጋ
ለመድከም አልሻም፣ ለዚህ ፈራሽ ሥጋ።
ያስገመግም ነጐድጓድ፣ ጣሪያው ኡ - ኡ - ይበል
ሰርጎ ይግባ ብርዱ፣ በቁርጥማት ልዛል!
የታል ብቸኝነት? በሹል ጥፍሩ ይውጋኝ
ልወረር በስቃይ፣ ይመመኝ - ይመመኝ።
ይዘርጉ እልፍ እጆች፣ በጉጠት ልሟጠጥ
ይንሰፍሰፍ አንጀቴ፣ በእንግልቱ ልናጥ
ሊያልፍልኝ ሲያባራ፣ አይገባኝም መሮጥ።

ሚያዚያ 08/1997 ዓ.ም

*ወደድኩኝ ድጋሚ

ምን ሆነ መሰለሽ . . .
ነበረኝን ስሸኝ፣ አለኝን ሳመጣ
አለኝንም ስሸኝ፣ ሰው ገብቶ ሲወጣ
ነበረ ስጋቴ፣ ጣዕም እንዳላጣ።
የመጨረሻዬ፣ መጀመሪያ ሆና
የሰው ፊት ሥቆጥር፣ ባህሪይ ሳጠና፤
"የመጨረሻዬ" ያልኳትን አልፊ
ይኸው ላንቺ በቃሁ፣ በሕይወት ተርፊ።

2004 ዓ.ም

*የወደቀው ዘር

ከአርሻው ጠፋና ፍሬዬ፣
ርቆ ከደነኛው ማሣዬ፤
ከጭንጫው መሬት ወድቆ፣
ከሚኖረው ከሾህ ታርቆ
(ወፎች ጐጆ ከሠሩበት)
ካልዘራሁት ዳዋ ዘልቆ፤
(መፈናፈኛ አጥቶ አየሁት)
እንዳያድግ በሾህ ታንቆ።

*የሆድ አምላክ

ለማግኘቱ፣ ለማጣቱ
ለመውዛቱ፣ ለመንጣቱ
"እንጀራ" ነው ለሀበሻ፣ "እህል ውኃ" ምክንያቱ።።
ሕልውናው የጸናበት፣ መወጣጫ መሰላሉ
"የሆድ አምላክ" ተቀብቷል፣ ይገለጣል "በእህሉ!"
ለረገጠው መሬት ሳይሆን፣ ከእግሮቹ በታች ላለው
ለማይነካው ሲንጠራራ፣ ለሰማይ ነው የቀረበው።።
"እህል ውኃ" በሀበሻ፣ አምላካዊ ከብር ለብሶ
"በጡር አለው" ተሰቅዞ፣ "በክቡር ነው" ተወድሶ
ተሰዋቶ ነው ለሰማያት፣ የሚዘራው ምድር ታርሶ
"የሆድ አምላክ" ካለበቱ፣ ከእኛው ሀገር ምግብ ነግሦ።።

* * *

የት ነው ያለህ፣ የሆድ አምላክ?!
ላገሠህ ምን አደረክ?!
ላመለኩህ መች አጠገብክ?!
ምስመንህ ጠኔ ጥሎት፣ የሚበላው ተቸግሮ
በእርጥባን መኖር በቅቶት፣ ሀገር ላገር ተሟዙሮ
"የሆድ አምላክ" እውነት ካለህ፣ እስቲ ይጥገብ ለዘንድሮ?!?

2003 ዓ.ም

*በግ፣ ሣር እና
በግ

በፊት . . .
በግ ነበርን፣
ሣር ቅጠሉን የቃረምን።
አሁን . . .
ሣር ሆነናል፣
በጎች ይታዩናል።

*የመስከረም ናፍቆት

በጨለማ ስንዝ ሣለ፣
'ርቂ ብርሃን ፍለጋ
በቀቢጸ - ተስፋ ተይዤ፣
እየተናጥኩ ከራሴ ጋ
በኔው ያ'ሳብ ማዕበል፣
እኔው ከእኔው ስላጋ..
ጷግሜ ባቅሟ ረዘመች፣
አልገባ አለ የታል በጋ!¿?
በጷግሜ እና መስከረም መሀል
አንድ ሌሊት ብቻ ቀርቷል፤
እንዳይገባ አዲስ ዓመት፣
ዋዜማውን አቁሞታል!

* * *

ቅንጣት እውነት ማግዘፍ ችዬ፣
የጊዜን ሕግ ማመን ችዬ፣
ትዝታዬን ወዲያ ጥዬ፣
ፊቱን ሳስብ ከኋላዬ...
መሸቶ ነበር፣ ይኸው ነጋ
ከረምት ነበር፣ ጠባ በጋ
ሁሉም ነገር ተዘነጋ፤
ተዘጋ!

ጷግሜ 2004 ዓ.ም

*ሙሉ ጨረቃ በእኩለ ሌሊት

ደሜ በውስጤ ሲናወጥ፣
ስሜቴ አቅሉን ሲያጣ፤
ወንድነቴን ምን አገኘው?
ምንስ መራው ወደቁጣ?!

* * *

ገባኝ መሰል ተረዳሁት
ወገግታውን እንዳየሁት።
በመኝታ ቤቴ መስኮት፣
መጋረጃ በከለልኩት፣
ድል ነስቶታል ብርሃኑ-
ጨለማውን ባይ አጣሁት።

ለ...ካ...ስ

ይ'ቺ ሙሉ ጨረቃ
ከእንቅልፌ እንድነቃ፣
ዳብሳዋለች አካላቴን፣
በስሜት አንዝራ ደሜን
አስቆጥታ ወንድነቴን።
ጥሎኝ ሳለ ኃያል እንቅልፍ፣
በጥልቅ ስሜት ስንሳፈፍ፤

ደሞም...

ሰረቀ-ብርሃን ከመሬት
በሁለቱ ስበት ስሳርር፤
ወድቃ አየኋት ጨረቃን
ከጭንና ጭኔ ስር።

*የራስ ምስል ፮

አሁን ነኝ ጥያቄ፤
አሁን ነኝ፣ መልስ አልባ፤
አሁን ሰው የለኝም፤
አሁን አልጣባ።
አሁን ማንበብ ቀርቷል፤
አሁን ሰው መቁጠሩ፤
አሁን ብቻዬን ነኝ፤
አሁን ዝግ ነው በሩ።
አሁን ሰላም አለ፤
አሁን ቄንቄ አልፏል፤
አሁን ጥያቄ ነኝ፤
መልስ መሆን ቀርቷል፤
አሁን ብቻዬን ነኝ፤
የገባ ሰው የታል!?!

መስከረም
6 ቀን 1998 ዓ.ም

*ፍራ - ፍሬ

በስንክ - ሣር ሕይወት፣ እንግልትነቱ
ከቃል ጋር ሲጣባ፣ የሰው ማንነቱ
ተሸናፊ ' ኮ ነው፣ ለደራሽ ስሜቱ።።
የፍሬዋ መዘገዘ፣ ርግማነ - ቃሉ
"ኦ አዳም ለ - አዳም" ፣ በማፈር እንዲሉ፤
ፍራፍሬ . . . ፍራ፣
ፍራ . . . ፍራፍሬ
እየለየህ ብላ፣ ብስሉን ከጥሬ።።

*እችልሻለሁ ! !

ስለ እውነት አልሻለሁ፣
ስለወደድኩሽ እችልሻለሁ !
የአያሌ ሞገደኞች ድምር፣ በአንድነት ተጨፍልቆ
ከሰብአናሽ ተላቁጧልኝ አድርጎሻል የሴት ጎልቆ።
ካልተገሩ ባህርያት፣ እስከጠፉ ያለም ፍጥረት
ነፍስያና አመላቶች ተጎንጉነው ያየሁባት
ብትሆኝም ብቸኛዋ፣ እስከዛሬ ያፈቀርኳት
አልሻለሁ "አያሌዎች" ፣ ምስክር ነኝ ስለእውነት !
ይህም ቢሆን... "እችልሻለሁ ! "
ባንዲት ነፍሴ አምላለሁ !
ፍቅር ቀድሞ ገሎኛል፣ ስለምንስ አፈራለሁ ! ?
የምታደርጊውን አድርጊኝ፣ ይኸው ፊትሽ ቆሜያለሁ
እ - ች - ል - ሻ - ለ - ሁ - ! !

2004 ዓ/ም

*የቆጥ ላይ ቅስቀሳ ፪

እናንተ ዶሮዎች፣ ከቆጥ ላይ ሆናችሁ፤
አትቀስቅሱን በቃ! ስለፈጠራችሁ።
"ተነሡ" አትበሉን፣ አትጩሁ ማለዳ
"ተቀስቅሰን" ያልተሻነው፣
ወጥሮናል የዕንቅልፍ ዕዳ።
ቀስቅሶ ማስነሣት፣ ከሆነ ሕልማችሁ
አደባባይ ውጡ፣ ከቆጥ ላይ ወርዳችሁ።

ግንቦት 1997ዓ.ም

* ስበት

የሕይወት ጎዳና፣ ፈተናው የበዛ፤
መቆምም ይከብዳል፣
መሮጥን ላበዛ።
እንኳን ልብረር ብሎ፣
ከፍታውን መርጦ፤
ፈተና ነው መንዝ፣
መሬትን ቆንጥጦ።
እናም . . .
ቢበዛ መፈተን፣ በኃይለኛ ንፋስ፤
ደግሞም ከፍ ሲሉ፣
ውሽንፍሩ ቢብስ፤
መፍትሄው አንድ ነው፣
ካሰቡት ለመድረስ፤
ከፍታን ጨምሮ፣ ስበትን መቀነስ።

*አዳኝ እና ታዳኝ

ድመት አይጥን አይምር፣
አይጥም አትሞት ፈርታ
አሳዳጇ ይበላታል፣
አትዘነጋም ላንዲት አፍታ።

****

ለአዳኝ ይከብዳል፣
ምሽጉን ያበዛ
አይመች ለወጥመድ፣
አይያዝ በዋዛ!

****

ድመት እንደሆነች፣
ማድፈጥ ነው ልማዷ
ጠግባም አይተዋትም . . .
አይጥ ማሳደዷ።

****

አዳኝም ታዳኝ ነው፣
ገዳይም ተገዳይ
አይጥም ደፋር ናት፣
ድመትን እስክታይ።
ሁሉም በየመንጋው እንዳፈጣጠሩ
በሕይወት እስካለ አይቀር መቆፈሩ
አይጥ ለምሽጓ ድመትም ለነውሩ!

*ሕምምታው <ይታመቅ>

ባይታይ እግረ - መቅ፣
እጅም ባይታሰር
ዘምኗል ባርነት፣
በሀበሻ ሀገር።
ኑሯችን ባርነት፣
እስረኛ ነው ዜጋ
መግቢያው ቢከፈትም፣
መውጫው የተዘጋ።
በአድርግ አታድርግ፣
ነፃነት ተነፍጐ
ሃሳብ ላያሳውቅ፣
አንደበት ታሽጐ
ሰብዓዊነት ታስሯል፣
ፊጥኝ ተጠፍንጐ።
ቱማታችን ከንቱ፣
ሰሚስ ምን ፈየደ!?
የከበበን ቅዕር፣ የታል የተናደ!?
አሁን መጮህ የለም፤
ጩኸት የለው ፋይዳ
ሕምምታን ማመቅ ነው፤
እስከሚፈነዳ!

2004 ዓ.ም

*የተዘጉ በሮች

ተከፍቷል ይሉናል፤ ኢትዮጵያ በሮቿ፤
ተዘግቶ ቆመናል ፣ አሁንም ልጆቿ።
አጥር ዘሎ መውጣት፣
ወንጀል ነው ይሉናል፤
አፎች ቢከፈቱም፤ በሩ ግን ተዘግቷል።
ከመካከላችን፣ አጥሩን የደፈሩ፤
ጥቂቶች ቢያመልጡም፣
ብዙዎች ታሰሩ።
እኛ ፈሪዎቹ፣ ለሕግ የተገዛን፣
በራሳችን አገር፣
መውጫ - መግቢያ ያጣን፤
ማንኳኳት አልተውን፣
ወይ አልሄድን ጥለን፤
በቀቢጸ - ተስፋ፣ ታስረን በምን አልባት
አሁንስ ታከተን፤ በር በሩን ማየት።
አትበሉ "ክፍት ነው" ፣ በሮች ተቆልፈውም፤
ካልሆነም እንድፈር፣ ቅፅሩን እንገለለው።

2004ዓ.ም

*መዘር በተጣርሶ

ምድርን ተመልከቱ . .
መጠቃቷን ችላ፣
መበዝበዟን ችላ መበከሏን ችላ
ዛሬም ትዘራለች፣ኡደቷን ቀጥላ።
እኛን ተመልከቱ . . .
መንገድ ተሠራልን፣
ማለፍ ግን አልቻልን
ሕንፃ ሰደሩልን፣
ዕጣው አልወጣልን
ሀብታም አበዙልን፣
ግን፤ ጠብ አላለልን፤
ልክ እንደ ምድሪቱ፣ መከራውን ችለን
መዘር አቅቶናል፣ እሷን ተከትለን።
እና በዚህች አገር፣ እውነታው ተጣርሷል
አንድ ሀብታም በስሩ፣ ሺህ-ዎች ያደኸያል
ድህነቱን እንጂ፣መች ሀብቱን ያወርሳል? !

2004 ዓ.ም

*አምልኮ

ጠላ ተጠጣና አተላው ተደፋ
ከጥራጊው ጋራ አብሮ እንዲከረፋ።
ከቤት ወደውጪ የጣለው አውጥቶ
ያስፈራራው ጀመር ሲያየው ጋራ ሠርቶ።
ቀትርን ከመጋኛ በአንድ አቆራኝቶ
መንገዱን ሰበረው የሰይጣን ቤት ሠርቶ።
ለኮንትራት ሕይወት ስንሞት ለሚያከትመው
ቤተ-ሠሪ ሆኖ እርሱ ቤት ሳይኖረው
ለጣለው ቆሻሻ ለደፋው አተላ
ሰው ሞኙ ይለፋል
ምስ፣ ግብር ሲያበላ!

6/06/98ዓ.ም

*ታኞቹ ተበሉ

ሲለው ካባ ለብሶ፣ ሲሻው ካባ አውልቆ
ሲሻው አፈር መስሎ፣ ሲሻው ተብረቅርቆ፤
ሲሻው ካኪ ለብሶ፣ ሲሻው ቁምላ ታጥቆ
ከዘመን ተማስሎ፣ ከበላይ ተጣብቆ፤
ሥሩን እያጠቃ፣ ሥርዓቱን ዘልቆ፤
ያልበላው ከበላው ፣ እየተቃበሉ
ሶስት ሺህ ዓመታት፣ ታኞቹ ተበሉ !

2004ዓ.ም

*የራስ ምስል ፪

አሁን
ፊልማውን፤
ያ—ን ሠ—ፊ ፊልማ!
ቤቴ እንደገባሁ
ቀድሞኝ ነበርና ጐጆዬን የያዘው
በመብራት ገደልኩት!
(እኔ ውስጥ እንዳለሁ)
ስማይ ማንጋጠጡ፣ ቆሜ በፊልማ
ለቁራጭ ከዋክብት፣ ብርሃን ስጠማ
መቆራቆዝ ትቼ፣ ከእራስ ኩርኩማ፣
አሁን ብቻዬን ነኝ፣ ከራሴ ልስማማ
ሕይወት እንደሆነ፣ ዙሪያው የማቅ ሸማ።

ግንቦት
11 ቀን 1998 ዓ.ም

*ድንቄም ሰንኮፍ ነቃይ

የልቤ ላይ እባጭ
የዕኩይ ምግባር ምጣጭ
አንጀቴን ከሚላጭ፣-
ይፍረጥ፣
ይንቆርቆር ወደውጭ
ያውክ፣
ከነፍሴ ጋር ይጋጭ
ልርጠብ፣
መርዙ ላዬ ይረጭ!
እንድታመም ሰናጥ
ዕባጩን ሳያፈርጥ፣
ማስታገሻ ሰጥቶ
ድንዛዜን ወግቶ
በሚያሽለኝ ሀኪም
ላፍታ ከማገግም...
ይንግ፣
ይውጣልኝ ገንፍሎ
ይንደድ፣
ይሂው ቤሳ ግሎ።
ልቤ እንዲያገግም
ድኖ ከነገር ግም
ከራስ በላይ ሀኪም
የለም! የለም! የለም!
የለም አለታከም!
ዞር በሉ ከፊቴ!
ቁስሌን ሰው አይጠብ
ሥራው ሀሞት ማለብ
መራር ውስጥን መስለብ፤

እንደ መርዛም ተባይ
ተናድፎ ዞር ባይ
አንዳች እባቄ አብቃይ
ድንቄም ሰንኮፍ ነቃይ!
ይቅር!
በሰው አልታከም
እኔ እንደሁ ለራሴ
ፈፅሞ አላንስም
ከራስ በላይ ሀኪም
የለም! የለም! የለም!

07/07/98

* ጡት እንዴት ይጣላል? !

የዋኋ እናቴ፣ እንዳልጠባ ብላ፣
ሬት ቀባች ጡቷን፣
መሮኝ እንድጠላ።
“ጡት ጣለ” -
ተባለ፤
ዘዴዋ ሰመረ፥ -
ተሞኝታ እንጂ፣
አድጌስ መች ቀረ! ?
ጓኑቼ ለወተት
የቀመስኩት ሬት፣
ውስጤን አኮማትሮት
ያ- -ኔ ያነባሁት . . .
አድጌም አልቀረ፣
ዛሬም አልጠላሁት።
እርም የለሹ ልቤ፣ ወተቱን ፍለጋ
ሬት አያግደው፣ ጡት እንዳይጠጋ፤
ሲያለቅስ አድሮ መሮት ፣
ይረሳል ሲነጋ።

*የራስ ምስል ፫

ልጅ ሆኖ ከልጆች፣ እራሱን አግልሎ
አድጐ ሲያይ ማያጉን፣
ትላንቱን ዞር ብሎ፤
ዛሬም ላይ ያልቆመ፣
ትላንትም ያለፈው
ሁሌም ወደ ነገ፣
ሲሮጥ የደከመው፣
ከመሰሎቹ ጋር፣ ፈልጎ እንዳላጣው
አገኘው ከቤቱ፣ ሲቆዝም ለብቻው።

ሀምሌ 28 ቀን 1998ዓ.ም

*እኔ እና እኔ

ውስጤ እንዲህ አለ...

"በአንድ እግሩ የሚቆም፣ በአንዱ ይደገፋል
ያጠፈው ሲደገፍ፣ የቆመው ይረግጣል
ሳይደገፍ ቋሚስ፣ ምን ያህል ይቆማል!?
አውራ ዶሮን ተመልከተው.....
ከሁለቱ አንዱን ሲያጥፍ፣
በረገጠው እግሩ ቆመ ፤ ያጠፈውን ሳያስደግፍ።"

ውስጤን እንዲህ አልኩት....

"ቢሳካለት ኖሮ ወደሰማይ መከነፍ
እናየው ነበረ ሁለቱንም ሲያጥፍ።"

ህዳር 2005 ዓ.ም

*ቀን በ"ቀን"

ተገድጄ ነበር በጨለማው ብርታት
ቤቴ የምገባው የምቆራኝበት።
የወፎቹን ዜማ የሚወደው ውስጤ
አስታውሳለሁኝ ገፋፍቶኝ መሮጤ
ከዕልመቱ ስቃይ ገላግሎኝ ከምጤ።
ትንፋሽ ከጨለማ ተቀይጠው ቤቴ
ሰላም እንዳላጣው ነፃ ከመውጣቴ ፤
ቀን ሲዘጋ ቤቱ የዋለው ተከፍቶ
ገና መሸት ሲል ከየትም ጎትቶ
"ፍቅር ነው " ይለኛል ጨለማን አጉልቶ።
የትላንቱ ትንፋሽ በጋራ የማጣጡት
ጠረን አልባነቱን እንደተረዳሁት፡-
(እኔ፣ ቤቴና ጨለማ)
መንጋቱን ጠላነው ከወፎች ስንሰማ
ቀን "በቀን" አወቅና !
ሰጥቶ እንደሚቀማ።

11-02-98ዓ.ም
ምሽት

*ይድረስ ለዱለኞች

ዱለኞች በርክተው፣ ትኾት ሆነ በትር
የቆመን የሚጥል፣ ጽኑን የሚሰብር።
ያወረን አጎበር፣ መልካሙን አያሳይ
ያስረን እሳቤ፣ ጭብጨባን አጣጣይ!
"አድናቆት መርዝ ሆኖ፣ ተደናቂን ገዳይ¡"
መቶ ለሚገባው፣ ዜሮ መሸለሙ፤
ዜሮ ለሚገባው፣ መቶ ማሸከሙ
ጥመት እንደ ማቅናት፣ ቀናውን ማጥመሙ፣
ፍሬ አፍርቷልና -
እናንተ ዱለኞች፣ "የምሥራች ስሙ!"
ደኽነኛው ማሳችን -
በጸዋ ተዋጠ፣ ፋፋልን አረሙ¡!¡

*የወህኒ ውስጥ ወህኒ

ገና ስንወለድ ፣ ስንበቃ ለምድር
ወህኒ ተዋለናል፣ በሞት ይፍታህ ሰፈር፤
ከዚህ ሰ - - ፊ ቅዕር፣ ከዚህ የ ' ሾህ አጥር
ዘመናት አልፈዋል፤ ሴት - ወንዱ ሲታጐር።
ከዕኑ እሥራት፣ ከሞት ይፍታህ ፍርዱ
ማምለጥ አይታሰብ፤ ተሰብሯል መንገዱ።
እግረ - ሙቁ ከርሮ፣ የታሰርንበቱ
በወህኒ ላይ ወህኒ፣ ሆነና ሕይወቱ
እርስ - በራስ አቆራኝቶ፣ ተብትቦናል ሥርአቱ።

“ትጠምቂልኝ ጀመር”

ለጠላሽ መጥመቂያ፣ ጋኑን አጥነሻል
ብቅል አብቅለሻል፣ አሻሮ ቆልተሽል
ጌሾ ቀንጥሰሻል፣ እንኩሮ አንኩረሻል...
* * *
ተጠጥቶ ሳያልቅ፣ ከጋን ያለው ጠላ
ቅራረው ሳይወጣ፣ ትጠምቂያለሽ ሌላ።
* * *
ያን ሰሞን ሳልጠጣ
በፍቅርሽ ሰክሬ፣ ስምሽን ክንዴ ላይ -
በመርፌ ስነቀስ
በምናብ ስቃትት፣ በቅናት ስጠበስ
አንቺም አትጠምቂ፣ እኔም ጠላ አልቀምስ።
የፍቅራችን እድሜ፣ በጨመረ ቁጥር
የጎሽ - ያልጎሽ፣ አንዳንዴም ፍሊተር
ጠላ በየአይነቱ፣ ትጠምቂልኝ ጀመር።

2005ዓ.ም

*የገደሉ አፋፍ

ድሮ . . .
አይኖቼን የላኩት፣
ታች ሆኜ ወደላይ
የገደሉን አፋፍ፣
መሥሎኝ ነበር የማይ።
ከላይም አልነበርኩ፤
ከታችም አልነበርኩ!
መውጣቱንም አልቻልኩ፤
እንዴትሥ ታች ወረድኩ?!
እንዳላልኩ . . .
ዘንድሮ -
ከዚያ አድማስ ማዶ፣
ለዓይን ዕርቆ፤
ወደላይ ሣንጋጥጥ፣
ፕሚያየኝ አዘቅዝቆ፣
የጥበቡ መብዛት፣
መሥፈርት የለሽ ህልቆ
"አለ" አልኩኝ ጠቢብ፣
አለ ከእኔ ፕርቆ!

ጥቅምት
2002 ዓ.ም

*የመተካከት ድግስ

ስብዕናችን ኮሰሰ
ብዝሀናችን አነሰ።
በ"ቱልቱላ" አኮሰሱን፤ የቃል አረሩ ነደደ
ፊዩኘኒታችን በጥሩንባ አሳከረው፣
"ጥቂቶች" መባል ተለመደ።
ድምፃችን ሰሚ አጣ፤ ቀዳዳው ሁሉ ተደፈነ
"ተሰዋን" ያሉለት ዓላማ፤ ረግጦን መግዘት ሆነ
"ተረግጠ የጮኘ ይጨፍለቅ!"
በሚሉት ስልት ታፈነ!
እናም እንዲሁ ሆነ . . .

ስብዕናችን ኮሰሰ
ብዝሀናችን አነሰ።

አገር "በኔ ልብላው" ተሞላ፤ ትውልድ ለግሉ ነፈገ
ተሰፋ እንደዝናብ ነበረ፤ ድንገት አርጥቦን ሰረገ።
በትግል ለተጣለው ሰንጋ፣ የጠጅ በርሜል ተመረገ
ለሕዝብ በታሰበው ዳስ፣ ለወዳጅ ዘመድ ተሰረገ፤
በርሃ ያከሰለው ገላ፣ ማግስቱን ለብቻው ፈለገ።
ብዙሐኑን አኩሰሰው፤ "እልፍነታቸው" ተለፈፈ
አቁማዳችን ተራቆተ አገር በሃፍጥ ነጠፈ።

"በትግል" በጣሉት ሰንጋ፣ ለዓመታት ተደገሰ

እናም እንዲሁ ሆነ
የበርሜሉ ምርግ ፊረሰ፣
ጥም በጠጅ ተከላ፣ አፍም በሙዳ ታበሰ።

"መተካካት" ተቀመረ፤ ለርዝራዥም "ዋስ" ሆነ
እግር በእግር ተረገጠ፤ ተረጋፊ ዛሬም ለመነ...

እናም እንዲሁ ሆነ
ብዝሕነታችን እንደቀለለ
ድግሱም እንዲሁ ቀጠለ።

ሚያዚያ 19ቀን 2005ዓ.ም

"ሀ-አይሞትም "ለ"ም ገና ይወለዳል!

ቱዋ (ጋርጋንቱዋ) አዲስ አድማስ ጋዜጣ

"...ሄኖክ እና "ሀ-ሞት" እኔን የቀሰቀሱኝ ወደ አንድ መልዕክት ነው። "አሁንም የበፊቶቹ አይነቶች አሉ" ወደሚል ንቃት ተቀሰቀስኩኝ። በትጋት መከታተል አለብኝ ከእንግዲህ። ገጣሚዎች አሁንም አሉ። "ሀ ቢሞት "ለ" ይወለዳል። ውልደት ካለ ደግሞ ሞት አለ።

"... ሲሞት ደግሞ ትክክለኛ ውልደት መኖሩ አረጋጋጭ ነው። ሄኖክ ወደ ሞት የሚያደላ አለመሆኑን "የሽንታችን ውጤት"፣ "እኔ ሰራሽ ሃውልት"፣ "ሃውልቱ ይበላ" የሚሉ ግጥሞቹ ገላጭ ናቸው። ሃውልት የሞቱትን መዘከሪያ መሆኑ አያጠራጥርም። ሃውልት ቆፍሮ ለማውጣት የሚታገሉት ከውልደት ጋር አንድነት የላቸውም። ከውልደት ጋር አንድነት የሌላቸው ገጣሚያን ሞልተዋል። ሞልተዋል ብቻ ሳይሆን፤ በጥበብ ወጣትነት ትኩስነት ቋንቋ አንባር "ሞተዋልም"። ታሪክን ለማዋለድ የሚጥር፤ ራሱን ለማዋለድ ከሚጥር ጋር የዘመን ልዩነት ይፈጥራሉ። ራሱን ለማዋለድ ከሚጥር ደግሞ እውነትን ለመውለድ የሚጥር የመሞት እድሉ ጠባብ ነው። የወለደው እውነት ወቅትን፣ ጭሰን፣ ሃይማኖትን ወይንም ሌላ ጊዜያዊ አጥርን መሰረት ያደረገ እስካልሆነ ድረስ። ይህንን የተሳካ ውልደት ማከናወን የቻሉ ጥቂቶች ናቸው። ሃውልት አይሆኑም።

"...ሄኖክ ወደ ፊት የሚያደላ ገጣሚ ነው። አጥንት ለቃሚ፣ መቃብር ቆፋሪ፣ ሃውልት አምላኪ አይደለም። "ቀን መቼ ይቆማል" በሚለው ግጥሙ ይሄንን ማለቱን እርግጠኛ ነኝ። ...በትልቁ እስር ቤት (ውልደት/ሞት) መሀል ቤት ካለው የፖለቲካ ስርዓት እስር ቤት አንባር የእግረ ሙቁን ድርብርብ እያወዳደረ ይመዝናል። ወደ ሜታፊዚክሳዊው እስር ቤት ሳይሆን ወደ የስርዓቱ እስር በበለጠ ይጮኻል። ምናልባት የህይወት እስር ቤት ከውልደት በኋላ ቢጨሁም ከሞት በስተቀር መፍትሔ ስለሌለው ይሆናል።

"የፖለቲካ (የስርዓት) እስር ቤት ግን ለማሻሻል ይቻላል። ነፃነቱን በሚፈልግ... እና የሚፈልገውን መግለጽ በቻለ የሰው ነፍስ አማካኝነት የሚያስተጋባ ጥርት ያለ ጩኸት አለ። የሄኖክ ስጦታው የግጥም መድበል የዚሁ ፍላጐት መግለጫ ይመስላል። ... "ታኞቹ ተበሉ" የሚለው ግጥም፤ ለሰው ልጅ ጭቆና የተሣፈ ቢሆንም፤ የሚገልፀው ግን በዓለም ውስጥ ስላለው የሰው ልጅ በአጠቃላይ ከመሆን ይልቅ ለሀገራዊ የሰው ልጅ የተንጣጠረ ነው። ወደ General ሳይሆን practical። ለሦስት ሺ አመት የተፈራረቀው መልክ ብዙ ጨቋኝ ዛሬም አለ እያለ ነው። እየተለዋወጠ የሚደጋገመው ሽራፋ ፍትህ ግን እንዲቀየር ፍላጐቱ ነው። ገጣሚው፤ "መቼስ ምን ይደረጋል!" እንደ

ሽራፋነቱ እውነታውን እንቀበለው የሚል አይደለም። ገጣሚው የጐደለውን እውነት የሚያስሰው በሌላ ማንም ቀዳሚ ላይ ተንተርሶ አይደለም። ከዚህ በፊት የቀደሙት ስህተት ከነበሩ፤ ዕርምት የሚመጣው ከራሱ ጋር እና ከውስጡ በወጣ እውነት ብቻ ነው። ይኼንንም እምነቱን በተለይ ከሚሊኒየሙ በፊት በነበሩ የራስ ፍለጋዎቹ ወይንም ፍላጐቶቹ ላይ በተደጋጋሚ ገልፆታል። ከቀደሙት ጋር በማጨብጨብ ከሚወለዱት ጋር መቆዘምን (በዚያ ወቅት) በዛፋቸው ግጥሞቹ ላይ መታዘብ ይቻላል። ለተለመደው ስህተት ከመከፈት...ላልተለመደው ግን የሚናፈቀው እስኪገኝ መከፋት እና ወደ ብቸኝነት መቆለፍን (መቆዘም) መርጧል።

"ይኼንንም በተለይ በ"ራስ ምስል" ፮፣፪ እና ፫ ቁልጭ አድርጐ ገልፆታል። . . .ሁሉንም ትቶ "ዘግቶ" ከተቀመጠ በኋላ ነው ወደ ሚሊኒየሙ "ከፍታን ጨምሮ" "ስበትን ቀንሶ" በሀይል የወጣው። ሲወጣ ይዞ የወጣው አንድ ድምጽ ነው፤ "ነፃነት" የሚል ድምጽ። ከሚሌኒየሙ በኋላ የዛፋቸው ግጥሞች የከረመውን ውሽት ለመጣስ የሚጮሁ የነፃነት ድምፆች ናቸው። ማጠቃለያ በዚህ በአጭር ማጠቃለያ ማለት የፈለኩት አንድ ነገር ነው። ውበት እና እውነትን መግለጽ ከሆነ የጥበብ ተልዕኮ...መጀመሪያ ግን እውነትና ውበትን ለማብቀል መሬቱ እና ከባቢ አየሩ በፍርሃት እና ግራ መጋባት ወይንም የሌላን አላማ ማስፈፀሚያ በሆኑ ያረጁ አስተሳሰቦች እና የጥበብ አመለካከቶች የተበከለ መሆን የለበትም። ከሆነ ደግሞ፤ ውበትን ፈጣሪው እና እውነትን ገላጩ፤ ከዚህ አሉታዊ ቀለበት (አስር ቤቱ) ሰብሮ መውጣት አለበት።

"ገጣሚው የሞከረውም ይሄንን ነው። ጥበብን ለጥበብነቱ ወይንም ውበትነቱ ከመጠበቡ በፊት በመሸንቆጥ ከሆነ አሉታዊውን መንፈስ የሚያባርረው የጥበብ ገለፃ ለዚህም ተግባር ታገለግላለች። ዋና ተግባሩዋ ይህ ሆኖ፤ ዋናውን ተግባር እንዳታከናውን የነፃነት አየር የሚያሳጥራት ደግሞ "ተራው" ከሆነ፤ ተራውንም ተራ ባልሆነ ሃይል... ጠበሏን ረጭታ ማባረር ትችላለች። የሄናከ ስጦታው (ተሰጥኦው) ይሄንን ማድረግ ነው። "ሀ" አይሞትም ገና "ለ" ይከተላል። ለገጣሚው (በአጠቃላይ) ተስማሚ የገለፃ ነፃነት አስኪፈጠር በድን መስሎ መቆምም መፍትሔ አይደለም። መሮጥን ማብዛት ነው የሚሻለው። ከፍታውን መርጦ። ገጣሚውም "ስበት" በሚለው ግጥሙ ይሄንኑ ይላል። የህይወት ጐዳና፣ ፈተናው የበዛ፣ መቆምም ይከብዳል፣ መሮጥን ላበዛ... ቢበዛ መፈተን በሃይለኛ ንፋስ፤ ደግሞም ከፍ ሲሉ፣ ውሽንፍሩ ቢብስ፣ መፍትሔው አንድ ነው፣ ካሰቡት ለመድረስ፣ ከፍታን ጨምሮ፣ ስበትን መቀነስ።"